የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 37
ADDIS ABABA 1ST June 2007

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፴፮/፲፱፻፺፱
የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስ ትሮች ምክር ቤት ደንብ .....................ገጽ ፫ሺ፮፻፴፩

CONTENTS

Council Of Ministers Regulations No. 136/2007
Dry Port Administration Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations . ............ Page 3631

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፴፮/፲፱፻፺፱
### የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አወጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፴፮/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>መቋቋም</u>

፩. የደረቅ ወደብ አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራው) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆ ጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 136/2007
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO ESTABLISH THE DRY PORT SERVICE ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2006 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Dry Port Administration Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 136/2007."

2. *Establishment*

1. The Dry Port Service Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as Public Enterprise.
2. The Enterprise shall be governed by the public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

The Ministry of Transport and Communications shall be the supervising authority of the Enterprise.

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የደረቅ ወደብ ሥራዎችን ለማካሄድና የሚከተሉትን አገልግሎቶች ለመስጠት ነው።

፩. የወጪና ገቢ ዕቃዎችን የመጫን፣ የማራገፍና የማከማቸት አገልግሎት መስጠት፣

፪. የወጪና ገቢ ዕቃዎችን በኮንቴይነር የማሸግና ከኮንቴይነር የማውጣት አገልግሎት መስጠት፣

፫. የኮንቴይነር ማስተናገጃና ማከማቻ አገልግሎት መስጠት፣

፬. ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ።

፮. ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፭፻ሚሊዮን (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ፲ ሚሊዮን(አስር ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን/፲፱፻፺፱

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch Office elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

The Purposes for which the Enterprise is established are to operate dry ports and:

1. to provide the services of loading and unloa-ding and storage of imported and export goods;
2. to provide the services of stowing and unpac-king of containerized export and imported goods.
3. to provide container depot services;
4. to engage in other related activities conducive to the achievement of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise is Birr 500,000,000 (Five Hundred Million Birr) of which birr 10,000,000 (Ten Million Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liabilit)*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 5th day of July 2007

MELES ZENAWI

Prime Minister of the Federal Democratic

Republic of Ethiopia